# የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የእምነት ባልደረቦች በመቻቻል ላይ ያሳዩት አቋም

# የአቡበከር አስሲዲቅ መቻቻል

እስልምና ለመቻቻል ትልቅ ቦታ የሰጠ ሐይማኖት ነዉ። የነብዮ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ)እና የእምነት ባልደረቦቻቸዉ የሕይወት ታሪክ በመቻቻል በታነጹ ተግባራት የተሞላ ነዉ።

ከዚህም መካከል አቡበከር አስሲዲቅ (አላህ ስራዉን ይዉደድለት)ለሙሰጠህ ኢብን ኡሳሳ ያሳየዉ ይቅር ባይነት አንዱ ነዉ። ቅርብ ዘመዱና ችግረኛ ስለነበረ ልገሳና እርዳታ ያደርግለት ነበር ስለ ልጁ አዒሻ አላህ ስራዋን ይዉደድላት በዉሸት ክብሯን ከነኩት አንዱ ነበር አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ከዚህ ትችት ነጻ ሲያወጣት አቡበከር አልስዲቅ እንዲህ አለ ``ስለ ልጂ ካወራ በኋላ ምንም አይነት እርዳታ አላደርግለትም`` ሲል አላህ ክብር የተሞላዉ ጌታ ይህችን አንቀጸ አወረደ :

**``ከናንተም የችሮታና የክብረት ባለ ቤቶች የሆኑት ለቅርብ ዘመዶችና ለድሆች በአላህም መንገድ ለተሰደዱ ስዎች ላይሰጡ አይማሉ፤ ይቅርታም ያድርጉ፤ (ጥፋተኞቹን) ይለፉም ፤ አላህ ለናንተ ሊምር አትወዱምን? አላህም መሐሪ አዛኝ ነው ።``**

**ሱረቱል ኑር፡22**

አቡበከርም አላህ ስራዉን ይዉደድለት በእርግጥ አላህ እንዲምረኝ እወዳለሁ በማለት ለሙሰጢህ ይሰጠዉ የነበረዉን እርዳታ መስጠት ቀጠለ **በአላህ ስም እምላለሁ መቼም አልከለክለዉም** አለ ቡኻሪ : 4141 ።

አቡበከር አስሲዲቅ የልጁንና የረሱልን ሚስት ክብር በነካዉ ዉሸት በጣም አዝኖ ነበረ ።ሃዘኑን የጨመረዉ ደግሞ ይህንን ዉሸት ያናፈሰዉ የገዛ ዘመዱ ሙሰጢህ ኢብን ኡሳሳ አል መጥለቢይ መሆኑ ነዉ።ይህም ሆኖ ግን ስሜቱን በመቆጣጠር ይህችን አንቀጽ በመከተል `` **ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው።`` ሱረቱል ሹራ : 40** ይቅር ባይነቱን አሳይቷል። እንደዚህ አይነት የላቀ ይቅር ባይነት ጠንካራ ህሊናና ጥሩ መንፈስ ያለዉ መልካም ሰዉ እንጂ ማንም አይደርስበትም።